# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና
# ልማት ኮሚሽን





## የህዳር ወር ዜና መጽሄት



ከሸማችነት ወደ አምራችነት!



ህዳር / 2018 ዓ.ም

**ዋና አዘጋጆች**

ወንድወሰን አካሌ

ፍቅር ስጦቴ

**ሌይአውትና ዲዛይን**

ፍቅረማርያም ይትባረክ

https://t.me/AAFarmersandUrbanAgriculture

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

@VoiceofAddisUrbanAgri

Farmeragr2020@Gmail.com

http://www.aafuadc.gov.et/

# ማውጫ


የተቋሙ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች ---------------------------------------------------------------------------------1

የኮሚሽኑ ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነት -----------------------------------------------------------------------------2

የከተማ ግብርና አዲስ አበባ ላይ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ---------------4

ዓለምን ወደ አንድ መንደር መቀየርና ለነቃ ማህበረሰብ መፈጠር የማህበራዊ ሚዲያ ትልቅ ድርሻ--------6

በማዕከሉ ውስጥ ሳሉ የወተት እና የሚደልቡ ከብቶች ክትባት ---------------------------------------------------7

ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ እና ሥጋ ዝውውር ህብረተሰቡን ለጤና ችግር ተጋላጭነት -----------------------------8

የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ለማዘመን የሚያግዝ አሰራር -------------------------------------9

በዓሉ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዐት ማእቀፍ የተገነባ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ----------------------------11

የተፋጠነ ዘመናዊ የሰብል ምርት አሰባሰብ ዘዴ ብክነትን አንጻር ------------------------------------------------12

ሙስና በማህበረሰቡ ቀደምት ብሂሎች ውግዝ ነው --------------------------------------------------------------13

ግብርና ከተፈጥሮ የተነጠለችውን አዲስ አበባ ከተፈጥሮ አንጻር ----------------------------------------------14

አርሶ አደሩ ከከተማዋ ልማት ጋር አብሮ ከመልማት አንጻር ------------------------------------------------------15

# የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

## ስለከተማ ግብርና ምን ያህል ያውቃሉ?

የከተማ ግብርና ልማትን በማስፋፋት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ በመፈናቀላቸዉ ተጎጂ የሆኑ አርሶ አደሮችን እና ቤተሰቦቻቸዉን ከደረሰባቸዉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ችግሮች ማላቀቅ እና በዘላቂነት ማቋቋም እንዲሁም የእንስሳት ጤና አገልግሎትን እና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንስፔክሽንና ሬጉላሪ አሰራርን በማሻሻል የህብረተሰቡን የበሽታ ተጋላጭነት መቀነስ እና አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ አርሶ አደርና ከተማ ግበርና ልማት ኮሚሽን ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናወናቸው ተግባራት ናቸው። ሁሉን አሳታፊ የሆነ የከተማ ግብርና ተጠቃሚነት እንዲፈጠር ደግሞ አግባብነት ያለው የኮሙዩኒኬሽን ተግባቦትን መጠቀም መተኪያ የሌለው ጉዳይ ነው።

የከተማ ግብርና ማለት አነስተኛ በሆኑ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የእንስሳት (የዶሮ፣ወተት፣ዓሣና ድለባ) የእፀዋት (አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት) ልማት በማካሄድ ማምረትና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበር፣ በማከፋፈል ጨምሮ ምርቱን ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለሽያጭ በማዋል ተጨማሪ የገቢ ምንጭ  እንዲፈጥር ያደርጋል።

ኮሚሽኑ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከግብ ለማድረስ እየሰራ ሲሆን እነርሱም የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ማቋቋም እና በቀጣይም አርሶ አደሩ ከከተማዋ ልማት ጋር አብሮ እንዲለማ ማድረግ፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በከተማው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ለከተማዋ የሚቀርቡ የግብርና ምርትና ግብዓት ጥራት እና ሃይጅን ተጠብቆ መቅረቡን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የተነሳ የኮሚሽኑ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትም እነዚህን መሰረታዊ አጀንዳዎች ለማሳካት የመረጃ ጥራትና ተደራሽነት ማስፋት እና የተቀናጀ የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ሥርዓትን ማሻሻል በዋናነት ትኩረት በማድረግ እየሰራ ይገኛል።

በመሆኑም የኮሚሽኑን መደበኛ ስራዎች እና ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታውን የዋጀ በተለያዩ የኮሙዩኒኬሽን አግባቦች ወቅቱን ጠብቆ ተዓማኒ የሆኑ መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል።

የከተማ ግብርና ጥቅም  ለህብረተሰቡ  በአነስተኛ ወጪ ትኩስ ጤናማና የተመጣጠነ የአትክልት ምግቦችን እንዲመገብ ያስችላል፤በዚህም ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል፤የሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲያድግና በራስ መተማመን እንዲጎለብት ያደርጋል፤ለሴቶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን የስራ

እድል እንዲፈጠር ያረጋል፤የመኖሪያ ግቢን እንዲሁም የአካባቢ ውበትን በመጠበቅ ሰዎች የእለት ተእለት ስራቸውን እና ውሎዋቸውን በተነቃቃ መንፈስ እንዲያሳልፉ ያስችላል፤የአረንጉዴ ሽፋንን ከፍ በማድረግ በከተማ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንዲቀንስ ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል፤በከተሞች የስራ አጥነትን ይቀንሳል፤በከተሞች የሚፈጠረውን የምግብ እጥረትና የዋጋ ውድነትን የቀንሳል፤የቤተሰብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭን በማሳደግ የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ይረዳል።

# የተቋሙ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች

## የተቋሙ ራዕይ /Vision/

በ2022 አዲስ አበባ የከተማ ግብርና የተስፋፋባትና የአርሶ አደሩ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት ከአፍሪካ ከተሞች በከተማ ግብርና ተምሳሌት ሆና

## የተቋሙ ተልዕኮ /Mission/

ህብረተሰቡን በከተማ ግብርና በስፋት በማሳተፍ ለከተማ የሚስማማ የኤክስቴንሽን ስርዓት ሥራ ላይ በማዋል፣ ጤናማ የሆነ የግብርና ምርት አቅርቦት በማሳደግ፤ በልማት ምክንያት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮችን በዘላቂነት በማቋቋም እንዲሁም ከችግር ተጋላጭነትን በመከላከል ከከተማው ዕድገት ጋር አብረው እንዲለሙ በማድረግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## የተቋሙ የአሰራር መርሆዎችና እሴቶች /

- ምግባችን ከደጃችን፤
- ፍትሃዊነት፤
- አገልጋይነት፤
- አሳታፊነትና አካታችነት፤
- ለላቀ ለውጥ ዝግጁነት
- ትኩረት ለአካባቢ ደህንነት፤

# የኮሚሽኑ ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነት

1.የከተማ የግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበት፣ ለገበያ የሚቀርብበትን እና የግብርና ልማት የሚጎለብትበት ስልት ይቀይሳል፤ ያስፈጽማል፤

2.ነዋሪዎች በከተማ ግብርና እንዲሳተፉ ያበረታታል፤ በተለያዩ የግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ምርትና ምርታማነታቸዉ እንዲጨምር ዘመናዊ የግብርና ግብዓት እንዲቀርብላቸው ሙያዊ ድጋፍና ምክር እንያገኙ ያደርጋል፤

3.የእንስሳት በሽታዎች ስርጭትን ያጠናል፤ በበሽታ ስርጭት የተነሳ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለመንግስትና ለአርቢዎች ያሳውቃል፤ ለእንስሳት አርቢዎች የእንስሳት ህክምናና የክትባት አገልግለት ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የዕብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፤ ታክመው መዳን የማይችሉ እና ባለቤት የሌላቸውን እንስሳት ያስወግዳል፤

4.ለእንስሳት አርቢዎች የማዳቀል አገልግሎት ይሰጣል፤ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለአርሶ አደር እንዲዳረስ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ይከታተላል፤ ለአርሶ አደሮች ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

5.የእንስሳት እና የዕጽዋት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤

6.የእንስሳትና የእጽዋት የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፤ በከተማው ውስጥ አገልግሎት ላይ ሲውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድሃኒቶችን ለሚያስወግድ አካል ያሳውቃል ፤

7.በመዋቅራዊ ፕላኑ ለእንስሳት፣ ለሰብል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ገበያዎችና ለከተማ ግብርና የተከለሉ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጁና በዘመናዊ መንገድ እንዲለሙ ያደርጋል፤

8.በግል የሚቋቋሙትን የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች፣ የቆዳና ሌጦ መጋዘኖች፣ ጸረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖችና መሸጫ መደብሮች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ደረጃና ጥራት ጠብቀው መስራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

9.በህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት እና በግል ቄራ ድርጅቶች የእርድ እንስሳትና የሥጋ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ሕገወጥ የእንስሳት እርድና በሕገወጥ መንገድ የታረዱ ስጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

10.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የመኖሪያ ቤቱ እስኪዘጋጅ ድረስ የቤት ኪራይ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

11.በልማት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተነሱ ተነሺ አርሶ አደሮችን ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በተሰጣቸው የክህሎት ሥልጠና መሠረት በአካባቢው በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ቅድሚያ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤

12.የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤ ለፕሮጀክቱ የሚያገለግሉ የማምረቻ እና የመሸጫ ማእከላትን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13.ኑሯቸዉ በግብርና ስራ ላይ የተመሠረተ አርሶ አደሮች የያዙት መሬት መጠን ልኬት እንዲወሰድና የባለይዞታነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል ፤

14.አርሶ አደሮች ባላቸው ይዞታ ላይ በግላቸው፤ ከአርሶ አደር ጋር በመደራጀት ወይም ከባለሀብት ጋር በመጣመር እንዲያለሙ አሰራር ይዘረጋል፤ ያስተባብራል፤ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

15.ምንም ገቢ የሌላቸዉና መስራት የማይችሉ አርሶ አደሮች ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማህበራዊና የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

16.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮች የተሰጣቸውን ካሳ አቀናጅተው ወደ ተሻለ ልማትና የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

17.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ የልማት ተነሽዎችን መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

18.የተሻለ ልምድና ሀብት ያላቸዉ ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦችን በመለየት አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በግል ይዞታቸው ወይም ተደራጅተዉ የሚሰማሩበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግበራዊ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

19.በልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደት መተግበሩን ይከታተላል፤

20.በልማት ስራዎች እና መልሶ ማልማት ተነሽ ለሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢውን የካሳ ግምት መተመኑን፤ የካሳ ክፍያ መፈጸሙን፤ ምትክ ቦታ መዘጋጀቱን፤ መሸንሸኑን፤ የምትክ ቤት ማግኘታቸውንና መቀበያ ሰርተፊኬት መሰጠቱን ይከታተላል፤

## የከተማ ግብርና አዲስ አበባ ላይ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ።

የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ የከተማ ግብርና ለኢኮኖሚው ዘርፍ ትልቅ አቅም እየሆነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን እያከናወነ ያለውን ተግባር በዴስክና በመስክ ምልከታ አድርጎ ለኮሚሽኑ ጀነራል ካውንስል ግብረ-መልስ ሰጥተዋል፡፡

የተከበሩ የም/ቤት አባላት በክብርት ወ/ሮ ተስፋነሽ ተፈራ ቡድን መሪነት እየተመራ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት እና ወረዳ አራት እንዲሁም አቃቂ ቃልቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ አምስት እና ዘጠኝ ላይ በመዘዋወር የመስክ ምልከታ አካሂዷል።

በመስክ የተመለከቱትንም በሪፖርት አደራጅተው አጥጋቢ ግብረ-መልስ ሰጥተዋል። ቋሚ ኮሚቴው በወተት ላም እርባታ፣ በዶሮ እርባታ፣ በንብ ማነብ፣ በማድለብ፣ በግቢና በጓሮ አትክልት እንዲሁም በሰብል ልማት የተከናወኑ ተግባራትን ተዘዋውሮ መመልከቱን ቋሚ ኮሚቴው በሪፖርቱ አመልክቷል።

አያይዘውም ቋሚ ኮሚቴው በጥንካሬ፣በጉድለትና ሊተኮርባቸው ይገባል ያላቸውን ጉዳዮች ለተቋሙ አመራርና ባለሙያዎች በሪፖርቱ አመላክቷል።

የኮሚሽኑ አመራሮች፣ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ እና የአቃቂ ቃልቲ ክፍለ ከተማ የዘርፉ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችም ቋሚ ኮሚቴው ቢያግዘን ያሉትን ሃሳብ በዝርዝር አስቀምጠዋል። የትራንስፖርት እጥረት፣ ኮሚሽኑ ወደ ቢሮ ከፍ ይበልልን የሚል፣ የእንስሳት መኖ ዋጋ፣ የአርሶ አደሮች መልሶ መቋቋምና መልማት፣ ጤንነቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርት ለማህበረሰቡ እንዲቀርብ ለማድረግ በተለይም ቄራዎችን ከማዘመን ጋር በተያያዘ፣ የግብዓትና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ችግሮች (እጥረቶች) እንዲፈቱልን በሚመለከታቸው አካላት እገዛ እንዲደረግልን በእናንተ በኩል ብታግዙን የሚል አስተያየትና ጥያቄ አቅርበዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተለይ ግብርና ሚንስቴር፣ ከተማ ልማት ሚንስቴርና ግብርና ባለስልጣን ተደራጅተው መጥተው ቢጎበኙን ከዚያም በሚጠበቅባቸው ልክ ዕንዲያግዙን በእናንተ በኩል አስፈላጊው ድጋፍ ቢደረግ ብለዋል።

የአርሶ አደር ማቋቋምና ልማት ም/ኮሚሽነር ወ/ሮ ሎኮ ዳለቻ ኮሚሽኑን ወክለው በቋሚ ኮሚቴው ለተደረገው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል፤ ከተማ ግብርና አዲስ አበባ ላይ አይቻልም የሚለውን አስተሳሰብ በመስበር እንደሚቻል ያሳየ መሆኑን ገልፀዋል፤ ቋሚ ኮሚቴው በመስክ ተዘዋውሮ በአርሶ አደር መልሶ ማቋቋምና ልማት፣ በእንስሳት እና እጽዋት ዘርፍ ላይ የተሰሩትን ስራዎች ተመልክቶ አስተማሪ የሆነ ሪፖርትና ግብረ-መልስ በመስጠቱ አመስግነዋል፤ በቀጣይም ድጋፍና ክትትላችሁ አይለየን ሲሉ አጽህኖት በመስጠት ገልፀዋል፡፡









የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ እና ምክትል ኮሚሽነር ሙሀመድ ልጋኔ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር በአርሶ አደር አይናለም እየተሰራ ያለውን የአሳ እርባታ እና ቦሌ ወረዳ1 የዶሮ እርባታና ከብት ማድለብ ማእከል ጎበኙ፡፡

ኮሚሽነሩ ከቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር እሸቱ ለማ ጋር በመሆን ባደረጉት ጉብኝት የአሣ እርባታው የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም የምግብ ፍጆታን በማሟላት በኩል ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ኮሚሽነሩ ገልጸው፣ የወረዳው እና የክፍለ ከተማው አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ጽ/ቤ ኃላፊዎችና ድጋፍ ለሚያደርጉ ባለሙያዎች ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ አሳስበዋል፡፡

በአርሶ አደር አይናለም እየተሰራ ያለው የአሳ እርባታ የስራ እድል ከመፍጠር አልፎ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ መስገኘት መቻሉን ገልጸው ከዚህም በላይ በሰፊው ማልማት እንደሚችል ተናግረዋል፡፡ ።

ሌላው የጉብኝቱ አካል የነበረው በቦሌ ክፍለከተማ ወረዳ1 በዶሮ እርባታና ከብት ማድለብ ዘርፍ የተሰማሩ የከተማ ግብርና ሥራው አካል የሆነው ማዕከል ለነዋሪዎቹ የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥና በኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ከማሳደግ አንጻር ቀላል የማይባል ሚና እንደሚጫወቱ ተገለጸ፡፡










## ዓለምን ወደ አንድ መንደር መቀየርና ለነቃ ማህበረሰብ መፈጠር የማህበራዊ ሚዲያ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን እንስሳት ልማት ልህቀት ማእከል ቡድን መሪዎች እና ባለሙያዎች በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም፣በቀውስ ጊዜ ኮሙኒኬሽን፣በህዝብ አስተያየት ቅሬታና አቤቱታ አቀባበልና መስተንግዶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልተና ተሰጠ፡፡

የስልጠናው አላማ መሰረታዊ የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት፣ ተግዳሮቶች፣ ጥቅሞች እና አጠቃቀም፣ የሥነ-ልቦና ጥቃቶችን መከላከል እንደሆነ ተነግሯል፡፡

አሳታፊነት፣ክፍትነት፣የጋራ ፍላጎቶችን ማንፀባረቁ፣ድንበር የለሽ እና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው መሆኑ፣ተለዋዋጭ ባህሪይ፣ማንነትን ደብቆ መንቀሳቀስ የሚያስችል መሆኑ፣ ውስብስብነቱ ፣መዋቅራዊ ስርዓት የለውም፣ኢንተግሬትድ (የብዙ ነገሮች ውህድ) መሆኑ፣እርስ በርስ የተሳሰረ መሆኑ፣ፈጣን እና በርካሽ ዋጋ መገኘቱ የማህበራዊ ሚዲያ ባህሪያቶች እንደሆኑ በሰነዱ ላይ ተመላክተዋል፡፡

ዓለምን ወደ አንድ መንደር መቀየሩ፣ገዥና ሻጭን በቀጥታ ማገናኘቱ፣ለቴክኖሊጂ ሽግግር ማገልገሉ፣የነቃ ማህበረሰብ ለመፍጠር ማስቻሉ፣መረጃ ለማግኘት፣ ለማሰራጨት እና ለማከፋፈል ማስቻሉ፣መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት ማስቻሉ፣ጋዜጠኞች የማይደርሱበትን ክስተት ለመዘገብ ማስቻሉ እና በቀላሉ ታዳሚዎችን ማማለል ማስቻሉ የመሳሰሉት የማህበራዊ ሚዲያ ጥቅሞች እንደሆኑ ዳይሬክተሩ አክለው ገልጸዋል፡፡

ለባዕዳን ባህሎች ወረራ ጥቃት ያጋልጣል፣የፖረኖግራፊ ፊልሞችን እና እንቅስቃሴዎችን ያስፋፋል፣አሳስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ፣አሉታዊ ግንኙነቶችን፣ የማጭበርበር፣ የሽብር እንቅስቃሴዎችን ያስፋፋል፣ስም የማጥፋት ዘመቻዎችን ያስፋፋል፣ የአገርን በጎ ገፅታ ያጠለሻል፣ስህተቶች/ክስተቶች ፈጣን የሆነ መጥፎ ግብረመልስ ይፈጥራል፣ማህበራዊ ሚዲያ አብዛኛው በምዕራባዊያን እጅ ስለሆነ ጥገኛ ያደርጋል፣የቅጅ መብቶችን መፃረር እና ከቤተሰብ መነጠል፣ ብቸኝነትን ማስፋፋት የማህበራዊ ሚዲያ አሉታዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡

በማህበራዊ ሚዲያው ዘርፍ የበላይነትን ማረጋገጥ የሚያስችል አቅም መፍጠር ከስልጠናው የሚጠበቅ እንደሆነ ስልጠናውን የሰጡት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት









## በማዕከሉ ውስጥ ሳሉ የወተት እና የሚደልቡ ከብቶች ክትባት ተሰጠ።

በእንስሳት ልማት እና ልኅቀት ማዕከል ለወተት ላሞች፣ ጊደሮች እና ለሚደልቡ የዳልጋ ከብቶች የጎርርሳ (Bovine pastuerolosis) በሽታ መከላከያ ክትባት ተሰጠ።

በሽታው በባክቴሪያ የሚመጣና የእንስሳቱን የመተንፈሻ አካላት የሚያጠቃ ሲሆን በድርቅና በተጨናነቀ ሁኔታ የመነሳት አጋጣሚ እንዳለው ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

ክትባቱ ከ3 ወር በላይ ለሆኑ ጥጆች እና ለክበድ ላሞች በዓመት ሁለት ጊዜ በመስጠት በሽታውን መከላከል እንደሚቻል የዘርፉ ባለሙያዎች ጨምረው ተናግረዋል።

በማዕከሉ በሁሉም ክላስተሮች ክትባት የመስጫ መርሃ ግብራቸውን ጠብቀው እየተሰጡ መሆኑ በሽታው ከመከሰቱ በፊት የሚመጣውን ሁለንተናዊ ኪሳራ መከላከል እንዲቻል እንደሚረዳ ይታመናል።







# ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ እና ሥጋ ዝውውር ህብረተሰቡን ለጤና ችግር ተጋላጭ ያደርጋል፡፡

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን እና ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ጋር በመተባበር ህገ -ወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውርን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ውይይት አደረገ፡፡

በመድረኩ የአዲስ አበባ ከተማ ልኳንዳ ነጋዴዎች ማኅበር አመራሮችና አባላት፣ የሥጋ ማጓጓዣ መኪና ባለንብረቶች ማህበር አመራሮችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን ህገወጥ የእንስሳት እርድና ሥጋ ዝውውር ላይ ያተኮረ ሰነዶች ቀርበው ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡

ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ እና ሥጋ ዝውውር ህብረተሰቡን ለጤና ችግር ሲዳርግ የሚችል፣ ፍትኃዊ ያልሆነ የንግድ ውድድር የሚፈጥር፣ እንደ ቆዳና ሌጦ ያሉ ተረፈ-ምርቶች ባግባቡ ተይዘው ለኢንዱስትሪ ግብዓት እንዳይውሉና እንዲባክኑ የሚያደርግ፣ ለአካባቢ ብክለት መንስዔ የሚሆን በመሆኑ ሁሉም በጋራ ሊታገለው የሚገባ ተግባር መሆኑን ፀጋ ለማ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ም/ክ ኮሚሽነር ፀጋ ለማ (ዶ/ር ) የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን እንዲሁም የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ በጋራ በመሆን ከተሳታፊዎች ለተነሱ ሀሳብና አስተያየቶች ምላሽ ሰጥተዋል ።

በቀጣይም ቅንጅታዊ ስራው ተጠናክሮ የሚቀጥልና ጥራቱን፣ደህንነቱና ሀይጅኑ የተጠበቀ ለተጠቃሚው እንዲደርስ በጋራ የሚሰሩ መሆኑን ተቋማቱ የጋራ አድርገዋል፡ ፡









## ቴክኖሎጅን በትክክል ከተጠቀምንበት የሰውን ልጅ ህይዎት ያቀላል፡፡

የቴክኖሎጅ ጥቅምና ጉዳት በሚል ርዕስ በወርቃማዋ ሰኞ መድረክ ላይ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

ቴክኖሎጅ የሰው ልጅ ህይዎትን ያቀላል፣ሰዓት ይቆጥባል፣የፈጠራ ችሎታን ያበረታታል፣መረጃን በቀላሉ ተደራሽ ያደርጋል በአጸዋት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት የሰብል ባለሙያ አቶ ተስፋየ ኪዳነ ማርያም በሰነዱ ላይ አንስተዋል፡፡ አያይዘውም ቴክኖሎጅ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ጉዳትም አለው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጆችን ጥገና ያደርጋል፣የስራ መደጋገምን ያስከትላል፣ለወንጀል መከሰት አስተዋጽኦ ያበረክታል፣የልጆችን ትኩረት ይከፋፍላል እና በአካል መገናኘትን ቀንሳል ተብሏል፡፡









## የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ለማዘመን የሚያግዝ አሰራር ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ነዉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የአገልግሎት አሰጣጥ መማክርት ጉባኤ ምሰረታ ተካሄደ፡፡ ተገልጋዮች በተሳትፎአቸዉ ከኮሚሽኑ ቀልጣፋ፣ ዉጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ አገልግሎት እንዲያገኙ በማስቻል ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ እና በከተማዋ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ የድርሻቸዉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነዉ መማክርት ጉባኤ መመስረት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የህዝቡን ቀጥተኛና ነጻ ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችል ወጥነትና ግልጽነት ያለው የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት፣የአጋዥ አካላትን መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ተቋማት ተሳትፎን ለማጎልበት የሚያስችል አሰራር ለመዘርጋት፣የአገልግሎት አሰጣጥ መማክርት ጉባኤ በመፍጠር በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ከተገልጋይ ጋር

በቅንጅት በመለየት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመፍታት፣በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ተግባራት ላይ የዜጋውን አቅም እና እውቀት በተገቢው መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል የሰነዱ ዓላማ እንደሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ምዘና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ስለሽ ወርቅነህ በሰነዱ ላይ አንስተዋል፡፡ በመጨረሻም የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ም/ክ ኮሚሽነር ፀጋ ለማ (ዶ/ር ) እና የጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበበ ከተሳታፊዎቹ ለተነሱት ሀሳብና አስተያየት ምላሽ በመስጠት የምስረታ ጉባኤው ተጠናቋል፡፡














## በዓሉ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዐት ማእቀፍ የተገነባ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ሥር እንዲሰድ ያደርጋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን "ዲሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ-ቃል ለ20ኛ ጊዜ የሚከበረውን የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ከአመራሮቹና ጠቅላላ ሰራተኞች ጋር አከበረ፡፡

"ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል የሚከበረውን የ20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በማስመልከት በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሥርዐት ማእቀፍ የተገነባ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ሰፊ የአስተምሮ ሥራ ለመሥራት እድል ይፈጥራል (አገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ምዘና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ስለሽ ወርቅነህ)።

ም/ኮሚሽነር ወ/ሮ ሉኮ ዳለቻ ዴሞክራሲ እንደ መንግስት አስተዳደር የሚገለፀዉ በዉክልና እንደሆነ ገልጸው በህገ-መንግስቱ ላይ ጥያቄ ያለው ሰው ለምክክር ኮሚሽኑ ሀሳቡን በጽሁፍ እንዲሰጥ መንግስት በሩን ክፍት አድርጓል ብለዋል፡፡

ዴሞክራሲ እንደ ባህል የኑሮ ዘይቤ አንዱ የባህል መገለጫ ፣የፖለቲካ ባህል ፣አንድ ማሕበረሰብ በአገሩ የፖለቲካ ጉዳዩች ላይ ያለዉን እምነት፣ ስሜት እና አስተሳሰብ የሚያጠቃልል ነዉ (አቶ ጌታሁን አበበ የጽ/ቤት ኃላፊ)፡፡









# የተፋጠነ ዘመናዊ የሰብል ምርት አሰባሰብ ዘዴ ብክነትን ያስወግዳል፡፡

የተፋጠነ ዘመናዊ የሰብል ምርት አሰባሰብ ዘዴ ብክነትን የሚቀርፍ፣ ቀጣይ ልማትን የሚያሳልጥ ነው፡፡በመሆኑም ለአብዛኛው አርሶ አደሮች ብሎም የሀገራችን አካባቢ ልዩ ትርጉም ያለው የመኸር ወቅት አርሶ አደሩ የአመት ልፋቱን፣ የድካሙን ዋጋ የሚሰበስብበት ወሳኝና ልዩ ትኩረት የሚሻ ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል ። ያም ሆኖ የሀገራችን የግብርና ዘርፍ አለመዘመን መገለጫ በሆነው ሗላ ቀር የምርት አሰባሰብ ሂደትና ትኩረት ማነስ ምክንያት አርሶ አደራችን የጥረቱን ያክል እንዳያገኝ ሲያደርገው ቆይቷል።

በተለይም ደግሞ በድህረ ምርት ወቅት የሚታየው ከፍተኛ ብክነትና የምርት ጥራት መቀነስ እንዲሁም ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት የሚከሰተው የሰብል ምርት ብልሽት የግብርናው ዘርፍ አሳሳቢ ችግሮች ሆነው ቆይተዋል ለእነዚህ ችግሮች ቁልፉ መፍትሄ የደረሱ ሰብሎችን ፈጥኖ መሰብሰብ በተለይም ደግሞ የግብርና ሜካናይዜሽንን በመተግበር በዘርፉ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የምርት አሰባሰብ ዘዴን መጠቀም ነው።





## ሙስና በማህበረሰቡ ቀደምት ብሂሎች ውግዝ ነው።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ22ኛው ጊዜ በሀገር አቀፍ ደግሞ ለ21ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ-ሙስና ቀን በዓል "ትውልድን በሥነ-ምግባር፤ ተቋምን በአሰራር" በሚል መሪ ቃል ከአመራሮችና ጠቅላላ ሰራተኞች ጋር የፓናል ውይይት አካሂዷል፡፡

ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ ሙስና ዘርፈ ብዙ መገለጫ ያለው ኢ-ሞራላዊ ተግባር በመሆኑ ግለሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ተቋምን ብሎም ሀገርን በእጅጉ የሚጎዳ ስለሆነ ሁላችንም ሌብነትና ብልሹ አሰራርን በመፀየፍ፣ በመታገል እና በመከላከል የበኩላችንን ሚና መወጣት ይገባል ብለዋል፡፡

በአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት "ሙስና" መቅሰፍት ነው። ጥፉት፣ ብልሹ፣ ግም፣ መበስበስ፤ መከራ"... እና በመሰል ነውርን በሚገልጡ ቃላት ይፈቱታል። ሙስና በሃይማኖታዊ አስተምህሮ ኃጢያት፣ በዓለማዊ ሕጎች ወንጀል የሆነ በማህበረሰቡ ቀደምት ብሂሎች ውግዝ ነው።

ኦክስፎርድ መዝገበቃላትም ሙስናን (Corruption) ከአለመታመን/እምነትን ከማጉደል፣ ምግባረ ቢስነት፣ ጉበኝነት እና በመሰል ቃላት ይገልፀዋል። ከዝቅጠትና ከመቆርቆዝ ጋር ያቆራኝዋል።

በመሆኑም ሙስና የማህበረሰቡን የሞራል፣ የሕግና ፍትሕ እሴቶች ይንዳል፤ የፖለቲካ ብክለት መገለጫ ነው፤ የነባር ግብረ ገባዊ እሴቶች መናድ ማሳያ ነው፤ ለማኅበረሰብ ሕልውና አደጋ ነው፡፡

ሌላው ሙስና ምቾት፣ ቅምጥልነትና ራስ ወዳድነት መንፈስ የተጠናወተው እኩይ ምግባር መሳበስ ነው። በጥቂቶች ብዙሃኑን የሚበክል ድርጊት ነው። እናም ኢ-ፍትሐዊነት፣ የግል ጥቅም አሳዳጅነት፣ ሥርዓተ አልበኝነት፣ አድልዎ እና የሞራል ዝቅጠት እንዲስፋፋ ያደርጋል።

ሙስና ድህነትን ያባብሳል፤ ሰብዓዊ መብትና ክብርን ይገፋል፤ የዳበረ ባህልን ይሸረሽራል፤ ዕድገትን ይጎትታል፤ ግጭት ይቀሰቅሳል፤ የመንግስትን ቅቡልነት እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ይፈታተናል።

የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ መርጋ ጢጣ ሙስና በተለያዩ መልኩ ሊተገበር የሚችል ብልሹ ተግባር በመሆኑ እንደ ኮሚሽን በተለይም ለሌብነትና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ናቸው ተብለው በተለዩ ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

አያይዘውም የኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች የትኛውንም ዓይነት የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባርና ዝንባሌዎች ስትመለከቱ ጥቆማ ብትሰጡን አስተማሪ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ የምናደርግ ይሆናል።

ዋና ኮሚሽነር አቶ ባዩ ሽጉጤ መልኩ ምንም ይሁን ምን ሙስና ጠንክሮ መስራትን የሚኮንን፣ ሳይሰሩ መብንላትን የሚያጀግን፣ የአጋርነትን ሞራል የሚሰብር፣ ሀገርን ለደህንነት ስጋት አደጋ የሚጥል፣ ኢንቨስትመንትን የሚያቀጭጭ፣ መረጋጋትን የሚፈትን፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ዘላቂ ልማትን የሚገታ በመሆኑ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀውን ተግባር በመፈፀም የተግባር ሰው ሆነን መገኘት አለብን በማለት አጽህኖት ሰጥተው ተናግረዋል።






## ግብርና ከተፈጥሮ የተነጠለችውን አዲስ አበባ ከተፈጥሮ ጋር እያስተሳሰረ ይገኛል።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከግብርና ሚንስቴር፣ ከሚዲያ ተቋማት፣ ከቅንጅታዊ ተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከN-GOs፣ ከተጠቃሚዎች ተወክለው ከመጡ አካላት እና ከኮሚሽኑ የሚመለከታቸው አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር በከተማ ግብርና ተግባርና ኃላፊነት እና እና በተሰሩ ሰው ተኮር ሥራዎችና ውጤቶች ላይ የፓናል ውይይት አድርጓል።

በውይይቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩት አካላት በመድረኩ ደስተኛ መሆናቸውን፣ እስካሁን ያላወቋቸውን ጉዳዮች መረጃ ማግኘታቸውን፣ ከተማ ግብርና ሰው ተኮር የሆኑ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን አንስተዋል።አያይዘውም አብረን ብንሰራባቸው መልካም ነው ያሉትን ጉዳዮች ጠቁመዋል።






## አርሶ አደሩ ከከተማዋ ልማት ጋር አብሮ እንዲለማ እየተሰራ ይገኛል፡፡

አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ገብተው ከከተማዋ ልማት ጋር አብረው እንዲለሙ በኮሚሽኑ በኩል አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው እንደሆነ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በመገኘት ምልከታ አድርገናል፡፡

በምልከታችንም የአቶ ከተማ መንግስቱ፣ አቶ አለማዬሁ ጉልማ እና አቶ መኮንን አሰፋን የሥራ እንቅስቃሴ ተመልክተናል፡፡

አቶ መኮንን አሰፋ ትምህርት ቤት ሰርተው ለመንግስት በማከራየት በወር ከ900,000 ያላነሰ ገቢ እንደሚያገኙ፣ ግሮሰሪ፣ የዶሮ እርባታ፣ የከብት ማድለብ፣ የወተት ላም እርባታ ላይ ተሰማርተው ከ41 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደፈጠሩም ገልፀውልናል፡፡

ሌላው አቶ መኮንን ከ3,000 በላይ ዶሮ እያረቡ ሲሆን በቀን ከ2,600 በላይ እንቁላል እንደሚያገኙ፣ አንድ እንቁላል በ17 ብር እንደሚሸጥ እንዲሁም ወተት ለአካባቢው ማህበረሰብ 90 በሊትር እያቀረበ እንደሆነ ገልጿል፡፡

በመስክ ድጋፍ ላይ ያገኘናቸው ኮሚሽኑ እና የክፍለ ከተማ ባለሙያዎች አርሶ አደሩ ወደ ኢንቨስትመንት በመግባት ከራሱ አልፎ ለከተማዋ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የበኩሉን ሚና እንዲወጣ የሚጠበቅብንን ሁሉ እያደረግን ነው ብለዋል፡፡

አርሶ አደሩ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገባ ከማድረግ ጋር ምን እየተሰራ እንደሆነ ያነጋገርናቸው የአርሶ አደር ልማት ቡድን መሪ ወ/ሮ ደግነሽ በደዊ ከ152 በላይ አርሶ አደሮች ለኢንቨስትመንት ሁኔታዎች እንደተመቻቸላቸው፣ 58ቱ በራሳቸው እና በኮሚሽኑ ድጋፍ ወደ ሥራ እንደገቡ ገልፀዋል፡፡

አያይዘውም የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ፣ ሙያዊና ቴክኒካል ድጋፍ የመስጠት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ችግሮቻቸው እንዲፈቱ የማድረግ ተግባራት መከናወናቸውን አንስተዋል፡፡

የአርሶ አደር ማቋቋምና ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ረጋሣ ባይሣ ቀደም ብሎ አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት አስበው ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚቀርቡላቸው ምርጫዎች ሦስት ብቻ ስለነበሩ እጅግ በጣም ሰፊ ችግር ነበረብን አሁን ላይ ከፕላንና ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር ከ18 በላይ ዘርፎች ፀድቀው በመምጣታቸው የተሻለ ነገር አለ ብለዋል፡፡

አቶ ረጋሣ ድጋፍ ከማድረግም ጋር በተያያዘ አርሶ አደሮቹን በመስክ በመገኘት፣ ቅንጅታዊ ተቋማት ጋ ቢሮቸው ድረስ በመሄድ፣ የሙያና የቴክኒክ ምክርና ድጋፍ በመስጠት፣ ግንዛቤና ስልጠና በመስጠት አርሶ አደሮቹ ወደ ኢንቨስትመንት ገብተው ከከተማዋ ጋር አብረው እንዲለሙ ሰፊ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን








